8100០250/65
12/7/2009

748/2013

ለከተሞች መልካም አስተዳደርና አቅም ግንባታ ቢሮ
ከ/ል/ቤ/ሚ/ር

ጉዳዩ፡ **የጸደቀ መመሪያ ስለመላክ**

7ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም የስፖንሰር አድራጊዎች መመሪያ ቁጥር 60/2009 ሆኖ ከየካቲት 15 ቀን 2009 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ እንዲሆን የጸደቀ መሆኑ ይታወቃል።

በዚሁ መሠረት የመመሪያውን ተፈጻሚነት እንድትከታተሉ የጸደቀ 1 ጥራዝ መመሪያ (ሰነድ) ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ አድርገን የላክን መሆኑን እናስታውቃለን።

ከሠላምታ ጋር

አምባቸው መኮንን (ዶ/ር)
ሚኒስትር

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Urban Development & Housing

ግልባጭ፦

- ለክቡር ሚኒስትር ዴኤታ ( የከተማ ልማት ዘርፍ)፣
- ለክቡር ሚኒስትር ዴኤታ ( የቤቶች ልማትና አስተዳደር ዘርፍ)፣
- ለሚኒስትር ጽ/ቤትና ሚኒ ካቢኔ ጉዳዮችቢሮ
- ለሕግ ዳይሬክቶሬት

ከ/ል/ቤ/ሚ/ር

(2) ለጽ/ቤት
13/07/09

(1) አቶ ነጠየ
12/07/09

810 መ 250/65
12/7/2009

ለከተሞች መልካም አስተዳደርና አቅም ግንባታ ቢሮ
ከ/ል/ቤ/ሚ/ር

ጉዳዩ፡ **የጸደቀ መመሪያ ስለመላክ**

7ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም የስፖንሰር አድራጊዎች መመሪያ ቁጥር 60/2009 ሆኖ ከየካቲት 15 ቀን 2009 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ እንዲሆን የጸደቀ መሆኑ ይታወቃል፡፡

በዚሁ መሠረት የመመሪያውን ተፈጻሚነት እንድትከታተሉ የጸደቀ 1 ጥራዝ መመሪያ (ሰነድ) ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ አድርገን የላክን መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

አምባቸው መኮንን(ዶ/ር)
ሚኒስትር

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Urban Development & Housing

ግልባጭ፡-

- ለክቡር ሚኒስትር ዴኤታ ( የከተማ ልማት ዘርፍ)፣
- ለክቡር ሚኒስትር ዴኤታ ( የቤቶች ልማትና አስተዳደር ዘርፍ)፣
- ለሚኒስትር ጽ/ቤትና ሚኒ ካቢኔ ጉዳዮችቢሮ
- ለሕግ ዳይሬክቶሬት

ከ/ል/ቤ/ሚ/ር

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የከተማ ልማት እና ቤቶች ሚኒስቴር

FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

MINISTRY OF URBAN DEVELOPMENT AND HOUSING

የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም

Ethiopian Urban Forum

# የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር

# 7ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም የስፖንሰር አድራጊ ድርጅቶች መመሪያ ቁጥር 748/2013

የካቲት 2009 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## መግቢያ

በኢትዮጵያ ፈጣን የከተሞች መስፋፋትን ተከትሎ የከተማ ነዋሪዎችንና የሌሎች ባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ በማጠናከር መልካም ተሞክሮዎችንና ልምዶችን በማስፋፋት የከተማ ልማት ፖሊሲውን እና የከተማ ልማት ፕሮግራሞችን ትግበራና ስኬት ማፋጠን ይቻል ዘንድ ቀደም ሲል ዓመታዊ የከተሞች ቀንና ሳምንት በመባል ተሰይሞ በተለያዩ ከተሞች አስተናጋጅነት በየዓመቱ በሀገር አቀፍ ደረጃ ሲከበር የቆየ ሲሆን በ2009 በጀት ዓመት የከተሞች ፎረም በሚል በዓሉን በጎንደር ከተማ ይከበራል፡፡

የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረምን በገንዘብም ሆነ በአይነት ድጋፍ እንዲያገኝ በማድረግ ከተሞች የልማት ስራዎቻቸውን የሚያሳዩበትና ገጽታቸዉን የሚገነቡበት፣ እርስ በእርስ የሚማማሩበት፣ ለኗሪዎቻቸው እና ለሌሎች ባለ ድርሻ አካላት አስፈላጊ መረጃ የሚሰጡበት እንዲሁም የኢንቨስትመንት፣ የኢንዱስትሪ፣ የቱሪዝም፣ የገበያ እና ሌሎች መስህቦቻቸውን የሚያስተዋውቁበት መድረክ በመፍጠር ለዕድገታቸው መፋጠን አጋዥ የሚሆኑ ግብዓቶችን እንዲያገኙ ማስቻል አስፈላጊ በመሆኑ የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም ስፖሰር አድራጊዎችን ሚና በመለየት በጎንደር ከተማ ለ7ኛ ጊዜ የሚከበረውን የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም የገቢ ማሰባሰብ ሥራው የሚመራበትን ስርዓት ለመደንገግ ታሳቢ በማድግ ተዘጋጅቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር "የ7ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም የስፖንሰር አድራጊ ድርጅቶች መመሪያ ቁጥር 748/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያስጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ:-

1) **"የክብር ስፖንሰር"** ማለት 7ኛዉን የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም በገንዘብም ሆነ በአይነት ድጋፍ በማድረግ የሚሳተፉ የመንግስት የልማት ድርጅቶችና ተቋማት ማለት ነው፡፡
2) **"የአንደኛ ደረጃ ስፖንሰር"** ማለት 500,000 ብር እና ከዚያ በላይ 7ኛዉን የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም ስፖንሰር የሚያደርግ ድርጅት ማለት ነው፡፡
3) **"የሁለተኛ ደረጃ ስፖንሰር"** ማለት ከብር 300,000 እስከ 499,999 7ኛዉን የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም ስፖንሰር የሚያደርግ ድርጅት ማለት ነው፡፡
4) **"የሶስተኛ ደረጃ ስፖንሰር"** ማለት ከብር 300,000 በታች 7ኛዉን የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም ስፖንሰር የሚያደርግ ድርጅት ማለት ነው፡፡
5) በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለፀው ሁሉ ለሴት ፆታም የሚያገለግል ነው፡፡

## 3. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በ7ኛዉ የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም በገንዘብም ሆነ በአይነት ድጋፍ በማድረግ በሚሳተፉ የግል ባለሃብቶች፣ የመንግስት የልማት ድርጅቶች እና ተቋማት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

## 4. ዓላማ

7ኛዉን የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም በተሳካ ሁኔታ እንዲከበር የሚያስፈልጉ ወጪዎችን መሸፈኛ የሚሆን የገንዘብና የዓይነት ድጋፎችን በማሰባሰብ ከተሞች የልማት ስራዎቻቸውን የሚያስተዋውቁበት ሁኔታን ለማመቻቸት ነው።

## ክፍል - ሁለት

## የስፖንሰር አድራጊ አካላት ደረጃና የሚያገኙት ጥቅም

## 5. የክብር ስፖንሰር

7ኛዉን የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም በገንዘብም ሆነ በአይነት ድጋፍ በማድረግ የሚሳተፉ የመንግስት የልማት ድርጅቶችና ተቋማት **የክብር ስፖንሰር ድረጃ** የሚያገኙ ሲሆን የሚከተሉትን ጥቅማ ጥቅሞች ተጠቃሚ ይሆናሉ።

1) 7ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረምን በማስመልከት በኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ቴሌቪዥን በሚተላለፍ ማስታወቂያ ላይ ለ3 ጊዜ የድርጅቱ ስም እንዲተዋወቅ ይደረጋል።
2) 7ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረምን ለማስተዋወቅ በሚዘጋጅ የከተሞች ልሳን ጋዜጣ ልዩ ዕትም ላይ የድርጅቱ ሎጎ እና መግለጫ በግማሽ የፊት ገፅ ላይ  በከለር ህትመት እንዲወጣ ይደረጋል።
3) በሁሉም የ7ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም ቀናት በመድረክ የማስተዋወቅ ስራ እንዲሰራለት ይደረጋል።
4) በዋናው የስነ ስርዓቱ መድረክ ላይ በሚዘጋጅ ባነር ላይ የድርጅቱ ሎጎ እንዲወጣ ይደረጋል።
5) በበዓሉ ወቅቶች የክብር እንግዳው (VIP) መግቢያ አግኝቶ እንዲስተናገድ ይደረጋል።
6) በፕሮግራሙ መዝጊያ ዕለት ከዘርፉ እውቅና ይሰጠዋል።

## 6. የአንደኛ ደረጃ ስፖንሰር

500,000 ብር እና ከዚያ በላይ ስፖንሰር የሚያደርግ ድርጅት **የአንደኛ ደረጃ ስፖንሰር** የሚያገኝ ሲሆን የሚከተሉት ጥቅማ ጥቅሞች የሚያገኝ ይሆናል።

1) 7ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረምን በማስመልከት በኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ቴሌቪዥን በሚተላለፍ ማስታወቂያ ላይ ለ3 ጊዜ የድርጅቱ ስም እንዲተዋወቅ ይደረጋል፡፡
2) 7ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረምን ለማስተዋወቅ በሚዘጋጅ የከተሞች ልሳን ጋዜጣ ልዩ ዕትም ላይ የድርጅቱ ሎጎ እና መግለጫ በ1/4 የፊት ገፅ ላይ በከለር ህትመት እንዲወጣ ይደረጋል፡፡
3) በሁሉም የ7ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም ቀናት በመድረክ የማስተዋወቅ ስራ እንዲሰራለት ይደረጋል፡፡
4) በዋናው የስነ ስርዓቱ መድረክ ላይ በሚዘጋጅ ባነር ላይ የድርጅቱ ሎጎ እንዲወጣ ይደረጋል፡፡
5) በበዓሉ ወቅቶች የክብር እንግዳው (VIP) መግቢያ አግኝቶ እንዲስተናገድ ይደረጋል፡፡
6) በፕሮግራሙ መዝጊያ ዕለት ከዘርፉ እውቅና ይሰጠዋል፡፡
7) ለኤግዚብሽን ማሳያ የሚውል 12 ካሬ ሜትር ቦታ ያለ ክፍያ እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡

## 7. የሁለተኛ ደረጃ ስፖንሰር

ከብር 300,000 እስከ 499,999 ስፖንሰር የሚያደርግ ድርጅት **የሁለተኛ ደረጃ ስፖንሰር** የሚያገኝ ሲሆን የሚከተሉት ጥቅማ ጥቅሞች የሚያገኝ ይሆናል፡፡

1) 7ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረምን በማስመልከት በኤፍ ኤም ሬዲዮ በሚተላለፍ ማስታወቂያ ላይ 3 ጊዜ የድርጅቱ ስም እንዲተዋወቅ ይደረጋል፡፡
2) 7ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረምን ለማስተዋወቅ በሚዘጋጅ የከተሞች ልሳን ጋዜጣ ልዩ ዕትም ላይ የድርጅቱ ሎጎ እና መግለጫ በ1/4 የመሃል ገፅ ላይ በጥቁርና ነጭ ቀለም ህትመት እንዲወጣ ይደረጋል፡፡
3) በሁሉም የ7ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም ቀናት በመድረክ የማስተዋወቅ ስራ እንዲሰራለት ይደረጋል፡፡
4) በዋናው የስነ ስርዓቱ መድረክ ላይ በሚዘጋጅ ባነር ላይ የድርጅቱ ሎጎ እንዲወጣ ይደረጋል፡፡
5) በበዓሉ ወቅቶች የክብር እንግዳው (VIP) መግቢያ አግኝቶ እንዲስተናገድ ይደረጋል፡፡
6) በፕሮግራሙ መዝጊያ ከዘርፉ እውቅና ይሰጠዋል፡፡
7) ለኤግዚብሽን ማሳያ የሚውል 12 ካሬ ሜትር ቦታ ያለክፍያ ያገኛል፡፡

## 8. የሶስተኛ ደረጃ ስፖንሰር

ከብር 300,000 በታች ስፖንሰር የሚያደርግ ድርጅት **የሶስተኛ ደረጃ ስፖንሰር** የሚያገኝ ሲሆን የሚከተሉት ጥቅማ ጥቅሞች የሚያገኝ ይሆናል፡፡

1) 7ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረምን ለማስተዋወቅ በሚዘጋጅ የከተሞች ልሳን ጋዜጣ ልዩ ዕትም ላይ የድርጅቱ ሎጎ እና መግለጫ በ1/4 የመሃል ገፅ ላይ በጥቁርና ነጭ ቀለም ህትመት እንዲወጣ ይደረጋል፡፡
2) በሁሉም የ7ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም ቀናት በመድረክ የማስተዋወቅ ስራ እንዲሰራለት ይደረጋል፡፡
3) በዋናው የስነ ስርዓቱ መድረክ ላይ በሚዘጋጅ ባነር ላይ የድርጅቱ ሎጎ እንዲወጣ ይደረጋል፡፡
4) በበዓሉ ወቅቶች የክብር እንግዳው (VIP) መግቢያ አግኝቶ እንዲስተናገድ ይደረጋል፡፡
5) በፕሮግራሙ መዝጊያ ከዘርፉ እውቅና ይሰጠዋል፡፡

## 9. የአፈፃፀም ስልትና ስነ-ምግባርን በተመለከተ

1) 7ኛውን የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም ስፖንሰር አድራጊ ድርጅቶችን ለማፈላለግ የተቋቋመው ንዑስ ኮሚቴ የ7ተኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም የስፖንሰር አድራጊ ድርጅቶች መመሪያ በማዘጋጀት በሚኒ ካቢኔ እንዲፀድቅ ያደርጋል፡፡
2) ንዑስ ኮሚቴው ስፖንሰር ሊያደርጉ የሚችሉ ድርጅቶችንና ባለሀብቶችን ዝርዝር ይለያል፡፡
3) ንዑስ ኮሚቴው ስፖንሰር ሊያደርጉ የሚችሉ ድርጅቶችንና ባለሀብቶችን የክብር ስፖንሰር፣ የአንደኛ ደረጃ ስፖንሰር፣ የሁለተኛ ደረጃ ስፖንሰር እና የሶስተኛ ደረጃ ስፖንሰር የሚያገኙትን ጥቅማ ጥቅም የሚገልፅ፣የቃል መግቢያ ቅፅ (Pledge form) እና የስፖንሰር ሽፕ እና የተሳትፎ ጥሪ ደብዳቤ እንዲደርሳቸው ያደርጋል፡፡
4) ንዑስ ኮሚቴው ስፖንሰር ለማድረግ ቃል ከገቡት ድርጅቶችንና ባለሀብቶችን ቃል የተገባውን ገንዘብ እስከ መጋቢት 30 ቀን 2009 ዓ/ም ገቢ እንዲደረግ ይከታተላል፡፡
5) ስፖንሰር ለማድረግ ቃል የገቡት ድርጅቶችንና ባለሀብቶች በገቡት ቃል መሰረት ድጋፍ በማድረግ ከተሞች የልማት ስራዎቻቸውን የሚያሳዩበትና ገጽታቸውን የሚገነቡበት፣ የኢንቨስትመንት፣ የኢንዱስትሪ፣ የቱሪዝም፣ የገበያ እና ሌሎች መስህቦቻቸውን የሚያስተዋውቁበት መድረክ በመፍጠር ለዕድገታቸው መፋጠን አጋዥ የሚሆኑ ግብዓቶችን እንዲያገኙ ለማስቻል አስፈላጊውን ድጋፍ በማድረግ የልማት አጋርነታቸውን እንዲወጡ ይጠበቅባቸዋል፡፡
6) ስፖንሰር አድራጊዎች መደገፍ የሚፈልጉት በገንዘብ ከሆነ ለዚህ ተብሎ በተከፈተው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም ስም በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አዲስ አበባ ቅርንጫፍ የባንክ ሂሣብ ቁጥር 1000191468655 ገቢ በማድረግ የባንክ ዲፖዚት ሰነድ ኮፒ ለኮሚቴው ሊሰጡ ይችላሉ፡፡
7) የዓይነት ስጦታ ከሆነ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የግዥ እና ንብረት አስተዳደር በሞዴል19 ገቢ በማድረግ ገቢ ያደረጉበትን ደረሰኝ ኮፒ ለኮሚቴው ይሰጣል፡፡

## ክፍል - ሶስት

## መመሪያውን ስለማሻሻልና የሚፀናበት ጊዜ

### 10. መመሪያውን ስለማሻሻል

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ይህን መመሪያ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘዉ ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

### 11. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከየካቲት 15 ቀን 2009 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አምባቸው መኮንን (ዶ/ር)

የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር ሚኒስትር

## 7ኛውን የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም ስፖንሰር አድራጊ ድርጅቶች የሚያገኙት ጥቅማ ጥቅሞች

| ደረጃ | ጥቅማ ጥቅሞች | የስፖንሰር ገንዘብ መጠን |
|---|---|---|
| የክብር ስፖንሰር | 1. 7ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረምን በማስመልከት በኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ቴሌቪዥን በሚተላለፍ ማስታወቂያ ላይ ለ3 ጊዜ የድርጅቱ ስም እንዲተዋወቅ ይደረጋል፡፡<br>2. 7ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረምን ለማስተዋወቅ በሚዘጋጅ የከተሞች ልሳን ጋዜጣ ልዩ ዕትም ላይ የድርጅቱ ሎጎ እና መግለጫ በፊት ገፅ ላይ በከለር ህትመት እንዲወጣ ይደረጋል፡፡<br>3. በሁሉም የ7ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም ቀናት በመድረክ የማስተዋወቅ ስራ እንዲሰራሉት ይደረጋል፡፡<br>4. በዋናው የስነ ስርዓቱ መድረክ ላይ በሚዘጋጅ ባነር ላይ የድርጅቱ ሎጎ እንዲወጣ ይደረጋል፡፡<br>5. በበዓሉ ወቅቶች የክብር እንግዳው (VIP) መግቢያ አግኝቶ እንዲስተናገድ ይደረጋል፡፡<br>6. በፕሮግራሙ መዝጊያ ዕለት ከዘርፉ እውቅና ይሰጠዋል፡፡ | |

| | | |
|---|---|---|
| **አንደኛ ደረጃ** | 1. 7ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረምን በማስመልከት በኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ቴሌቪዥን በሚተላለፍ ማስታወቂያ ላይ ለ3 ጊዜ የድርጅቱ ስም እንዲተዋወቅ ይደረጋል፡፡<br>2. 7ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረምን ለማስተዋወቅ በሚዘጋጅ የከተሞች ልሳን ጋዜጣ ልዩ ዕትም ላይ የድርጅቱ ሎጎ እና መግለጫ በፊት ገፅ ላይ በከለር ህትመት እንዲወጣ ይደረጋል፡፡<br>3. በሁሉም የ7ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም ቀናት በመድረክ የማስተዋወቅ ስራ እንዲሰራለት ይደረጋል፡፡<br>4. በዋናው የስነ ስርዓቱ መድረክ ላይ በሚዘጋጅ ባነር ላይ የድርጅቱ ሎጎ እንዲወጣ ይደረጋል፡፡<br>5. በበዓሉ ወቅቶች የክብር እንግዳው (VIP) መግቢያ አግኝቶ እንዲስተናገድ ይደረጋል፡፡<br>6. በፕሮግራሙ መዝጊያ ዕለት ከዘርፉ እውቅና ይሰጠዋል፡፡<br>7. ለኤግዚብሽን ማሳያ የሚውል 12 ካሬ ሜትር ቦታ ያለ ክፍያ እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡ | **ብር 500,000 እና በላይ** |
| **ሁለተኛ ደረጃ** | 1. 7ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረምን በማስመልከት በኤፍ ኤም ሬዲዮ በሚተላለፍ ማስታወቂያ ላይ 3 ጊዜ የድርጅቱ ስም እንዲተዋወቅ ይደረጋል፡፡<br>2. 7ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረምን ለማስተዋወቅ በሚዘጋጅ የከተሞች ልሳን ጋዜጣ ልዩ ዕትም ላይ የድርጅቱ ሎጎ እና መግለጫ በመሃል ገፅ ላይ በጥቁርና ነጭ ቀለም ህትመት እንዲወጣ ይደረጋል፡፡<br>3. በሁሉም የ7ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም ቀናት በመድረክ የማስተዋወቅ ስራ እንዲሰራለት ይደረጋል፡፡<br>4. በዋናው የስነ ስርዓቱ መድረክ ላይ በሚዘጋጅ ባነር ላይ የድርጅቱ ሎጎ እንዲወጣ ይደረጋል፡፡<br>5. በበዓሉ ወቅቶች የክብር እንግዳው (VIP) መግቢያ አግኝቶ እንዲስተናገድ ይደረጋል፡፡<br>6. በፕሮግራሙ መዝጊያ ዕለት ከዘርፉ እውቅና ይሰጠዋል፡፡<br>7. ለኤግዚብሽን ማሳያ የሚውል 12 ካሬ ሜትር ቦታ ያለክፍያ ያገኛል፡፡ | **ከብር 300,000 - 499,999** |

| | | |
|---|---|---|
| ሶስተኛ ደረጃ | 1. 7ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረምን ለማስተዋወቅ በሚዘጋጅ የከተሞች ልሳን ጋዜጣ ልዩ ዕትም ላይ የድርጅቱ ሎጎ እና መግለጫ በመሃል ገፅ ላይ በጥቁርና ነጭ ቀለም ህትመት እንዲወጣ ይደረጋል፡፡<br>2. በሁሉም የ7ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም ቀናት በመድረክ የማስተዋወቅ ስራ እንዲሰራለት ይደረጋል፡፡<br>3. በዋናው የስነ ስርዓቱ መድረክ ላይ በሚዘጋጅ ባነር ላይ የድርጅቱ ሎጎ እንዲወጣ ይደረጋል፡፡<br>4. በበዓሉ ወቅቶች የክብር እንግዳው (VIP) መግቢያ አግኝቶ እንዲስተናገድ ይደረጋል፡፡<br>5. በፕሮግራሙ መዝጊያ ዕለት ከዘርፉ እውቅና ይሰጠዋል፡፡ | ከብር 300,000 በታች |

# The 7th ETHIOPIAN URBAN FORUM SPONSOR'S BENEFITS

| LEVEL | BENEFIT | FEE |
|---|---|---|
| **Special Sponsor** | 1. 3 times name of organization Commercials on EBC /TV/<br>2. The logo of the sponsor will be included on news paper advertisements that will be made to promote the event.<br>3. The sponsor will be promoted every day of the event and every hour of the day between staged programs.<br>4. A banner holding the logo of the company shall be placed on the main stage<br>5. The sponsor shall be given seat during the opening of the event alongside the guest of honor<br>6 The sponsor shall be given a special prize at the closing ceremony of the event | |
| **FIRST GRADE** | 1. 3 times name of organization Commercials on EBC /TV/<br>2. The logo of the sponsor will be included on news paper advertisements that will be made to promote the event.<br>3. The sponsor will be promoted every day of the event and every hour of the day between staged programs.<br>4. A banner holding the logo of the company shall be placed on the main stage<br>5. The sponsor shall be given seat during the opening of the event alongside the guest of honor<br>6 The sponsor shall be given a special prize at the closing ceremony of the event<br>7 .The sponsor will be provided 12 square meters Exhibition space in the rub hall | **Br. 500,000 and above** |

| | | |
|---|---|---|
| **SECOND GRADE** | 1. 3 times name of organization Commercials on FM radio<br>2. The logo of the sponsor will be included on news paper advertisements that will be made to promote the event<br>3. The sponsor will be promoted every day of the event and every hour of the day between staged programs<br>4. A banner holding the logo of the company shall be placed on the main stage<br>5. The sponsor shall be given seat during the opening of the event alongside the guest of honor<br>6. The sponsor shall be given a special prize at the closing ceremony of the event<br>7. The sponsor will be provided 12 square meters Exhibition space in the rub hall | **Br. 300,000 - 499,999** |
| **THIRD GRADE** | 1. The logo of the sponsor will be included on news paper advertisements that will be made to promote the event<br>2. The sponsor will be promoted every day of the event and every hour of the day between staged programs<br>3. A banner holding the logo of the company shall be placed on the main stage<br>4. The sponsor shall be given a special prize at the closing ceremony of the event<br>. | **Below Br. 300,000** |

የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም
Ethiopian Urban Forum

To:

Addis Ababa

Dear Sir/Madame,

**RE: Invitation for sponsorship & participation**

As we are growing fast and moving to words the overall economic & social transformation, the urban development & housing sector has become increasingly instrumental specially in this particular GTP period and to which effort our ministry is in charge & responsible for the regularization, facilitation and all high level policy & strategic issues as for the urban good governance & capacity building, housing of all concerns (including in rural centers), development of micro & small scale enterprise (job creation& industry development) and the construction industry in general.

With this in mind, to foster realization of urban development and industrialization and coordinated efforts of stake holders of the sector has a paramount importance and as part of this concerted effort, our ministry has, therefore been organizing urban forums with growing urban agendas to help create innovative, competitive and conducive urban economic & social environment in Ethiopia.

Accordingly, we are already proceed with organizing the sixth "Ethiopian Urban Forum" under the Motto of **"Sustainable Urban Development & Good Governance for Renaissance"** to be held in Gonder City from April 29 th to 6th May of 2017. The event is aimed at enhancing awareness of the sector, recognizing public and private enterprises that have contributed to the development of industrialists, employment (Job creation,) innovation and over all sartorial development, venues for knowledge and experience sharing including sense of ownership of urban development amongst the public. It is also intended to create healthy & developmental competition among cities and promote the event into international level.

With this regard, your esteemed company is recognized as one of the firms playing important role in the comprehensive development endeavors of the country. The Ministry of Urban Development and Housing and the City Gov't of Gonder are, therefore, hereby cordially invite your good company to sponsor & participate in this important event against generous sponsorship benefits.

Hoping of your generosity& positive response, we remain,

Sincerely yours

Enc. Sponsorship package

C.C.

Technique Committee of the Ethiopian Urban Forum
M/U/D/H

የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም
Ethiopian Urban Forum

ለ
**አዲስ አበባ**

ጉዳዩ፡- **የስፖንሰር ሽፕ እና የተሳትፎ ጥሪ**

የከተማ ልማትና ቤቶች ሴክተር የሀገራችንን ራዕይ እውን ከማድረግ አንፃር የሚጫወተው ሚና ጉልህ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ በተለይም አሁን በያዝነው የልማት ምዕራፍ ከተሞች የኢንዱስትሪ ማዕከል እና የኢንዱስትሪያሊስቶች መፍለቂያ እንዲሆኑ ከማድረግ አንፃር ከፍተኛ ተልዕኮ ወስዷል፡፡ የተልዕኮው ስኬት የልማት ኃይሎች የጋራ እንቅስቃሴና ርብርብን የሚጠይቅ ሲሆን ከሁሉም በላይ የሰፊው የከተማ ነዋሪ ሕዝብ ንቅናቄና ስምረት ወሳኝነት አለው፡፡ ይህንን ንቅናቄ ለመፍጠርና ተልዕኮውን ለማሳካት በርካታ እንቅስቃሴዎች እየተደረጉ ሲሆን ከነዚህ መካከል አንዱ በየዓመቱ የሚከበረው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም ይገኝበታል፡፡

በዚህ መሠረት ዘንድሮ ለ7ኛ ጊዜ የሚከበረው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም ከዚህ በፊት ከነበረው በተለየ ሁኔታ የህዝብ ንቅናቄ በሚፈጥሩ አጀንዳዎች **"የከተሞች ዘላቂ ልማትና መልካም አስተዳደር ለህዳሴያችን"** በሚል መሪ ቃል ከሚያዚያ 21 እስከ 28 ቀን 2009 ዓ.ም. በጎንደር ከተማ ይከበራል፡፡ በዚህ በዓል በሴክተሩ አጀንዳዎች ዙሪያ በቂ ግንዛቤ የሚፈጠርበት፣ ለሴክተሩ እድገት ጉልህ አስተዋፅኦ ላበረከቡ የልማት ኃይሎች /ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት፣ የቴክኒክና ሙያ ተቋማት፣የማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት፡ ኮንትራክተሮች፣ ኮንሰልታንቶች፣የሪል እስቴት አልሚዎች፣ ሰፊ የሥራ ዕድል የፈጠሩ መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ዓለም አቀፍ ተቋማት፣ ወዘተ እውቅና የሚሰጥበት፣ ስኬታማ ልምዶችን መልካም ተሞክሮዎች የሚቀመሩበት አዳዲስ የፈጠራ ሥራዎች የሚበረታቱበት የህዝቡ የባለቤትነትና ተጠቃሚነት ስሜት የሚጐለብትበት እና ጤናማ የእድገት ውድድር በማካሄድ ግብረ መልስ የሚሠጥበት ይሆናል፡፡ በተጨማሪም ዓለም አቀፍ እውቅና እንዲያገኝ ጭምር የሚሠራበት ይሆናል፡፡ ስለሆነም በዚህ ከ200 በላይ ከተሞች በሚሳተፉበት ፎረም ላይ ድርጅትዎ /ተቋምዎ/ በሀገራችን ከተሞች ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ እና እድገት ዙሪያ ጉልህ ተሳትፎ ያለውና የልማት ኃይል አጋርነቱም ከፍተኛ በመሆኑ በኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም በዓልና በሚዘጋጀው ኤግዚቢሽን ላይ ቢሳተፍ ጠቀሜታው እጅግ የጐላ ይሆናል፡፡

በመሆኑም የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር እና የጎንደር ከተማ አስተዳደር በጋራ በመሆን ለዚህ ታላቅ እና ሀገር አቀፍ በዓልና ኤግዚቢሽን ቅድሚያ በመስጠት ስፖንሰር እንድታደርጉና እንድትሣተፉ ጥሪያችንን በአክብሮት እናቀርባለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

**ግልባጭ፣**

- ለኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም ዝግጅት ቴክኒክ ኮሚቴ
  ከ/ል/ቤ/ሚ/ር

አባሪ፡

- የስፖንሰርሺፕ ፓኬጅ ከዚህ ጋር ተያይዟል።



የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም
Ethiopian Urban Forum

## 7th ETHIOPIAN Urban Forum

## PLEDGE FORM

Name of the sponsor: ______________________________

Address :- Region ________City ____________ K/Ketema ______________

Kebele______________House No __________ Tel. ______________

Fax ________________P.O.Box ___________ E-Mai ____________

We confirm our agreement to take ______________________________ rank sponsorship against sponsor's Benefits as detailed the attached list and to pay a stated amount of Birr ______________________________/________ upon demand by the Ministry of urban Development & Housing.

| ________________ | ________________ | ________________ |
|---|---|---|
| Signature & seal | Name & Title | Date |

NB:

Sponsorship amount to paid in cash or transferred reemitted to the Commercial Bank of Ethiopia, Addis Ababa Branch Ministry of Urban Development & Housing — Ethiopian Urban Forum **Account No 1000191468655.**

የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም
Ethiopian Urban Forum

## 7ኛ የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም

## ቃል መግቢያ ቅፅ (Pledge form)

የስፖንሰር ስም ______________________________

አድራሻ፡-ክልል __________ ከተማ__________ ክ/ከተማ __________ ወረዳ/ቀበሌ __________

የቤት ቁጥር ______________ ስልክ ፡- የቢሮ ____________ ተንቀሳቃሽ ________

ፋክስ __________ ፖ.ሣ.ቁ. __________ ኢ-ሜይል ____________________

የ ______________________________ ደረጃ ስፖንሰር በመሆን በአባሪው የተዘረዘሩትን ጥቅማ ጥቅሞች ለማግኘት ብር ______________________________/__________ ለመስጠት ተስማምቻለሁ።

| ____________________ | ____________________ | ____________________ |
|---|---|---|
| ፊርማና ማህተም | ስምና ኃላፊነት | ቀን |

ማስታወሻ፣

ቃል የተገባውን ገንዘብ በተዘጋጀው ህጋዊ ደረሰኝ በእጅ ወይም በቼክ ሊከፈል ይችላል። አሊያም ለዚህ ዓላማ በከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም ስም በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አዲስ አበባ ቅርንጫፍ በተከፈተው የባንክ ሂሣብ ቁጥር 1000191468655 ገቢ ማድረግ የምትችሉ መሆኑን እንገልፃለን።

## ለ7ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም ስፖንሰር ሊያደረጉ የሚችሉ ኩባንያዎች ዝርዝር

| | |
|---|---|
| 1 | ብረታ ብረትና ኢንጅነሪንግ ኮርፖሬሽን |
| 2 | ኢትዮ ቴሌኮም |
| 3 | ብሔራዊ አልኮልና አረቂ ፋብሪካ |
| 4 | የኢትዮጵያ መድን ድርጅት |
| 5 | የኢትዮጵያ ምድር ባቡር ኮርፖሬሽን |
| 6 | የኢትዮጵያ መንገድ ኮንስትራክሽን ኮርፖሬሽን |
| 7 | ተገጣጣሚ ህንፃ አካላት ማምረቻ ድርጅት |
| 8 | መሶበ ሲሚንቶ ፋብሪካ ኃ.የተ.የግ.ማ |
| 9 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ |
| 10 | መከላከያ ዲዛይን ቁጥጥር ኢንተርፕራይዝ |
| 11 | የህንፃ ዲዛይን ድርጅት |